# አወይ ፖለቲካ!

(ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ)

አወይ ፖለቲካ! ወይ ነገረ መንግሥት!
ቀለም ለዋዋጩ፥ አወይ! አወይ እሥሥት!
አስጨራሽ እልህ፥ ተፈታታኝ ትእግሥት፥
ፈጥፍጦ የሚጥል፥ አዋራጅ በድል ማግሥት::

አወይ ገልበጥባጣው! አወይ ፖለቲካ!
ሃቀኛን የሚያረግ የተረሳ ላንቲካ፥
ቅኑን፥ ታኝኮ የተተፋ ማስቲካ፥
ለአላቲው የሚል "ድልን በወርቅ ሳህን እንካ"፥
እውነተኛን የሚያሰኝ እሱን በ'ጁ አይንካ፥
ሞላጫ የሚዝቀው ባካፋ፥ቀጥተኛ ግን በማንካ::

የከሃዲዎች ሙዚቃ፥ የቀጣፊዎች ቅንብር፥
አብሮ ጉዞ የማያስጨርስ፥ እስበስ የማያከባብር፥
ወዳጅ፥ ዘመድ በቁም የሚያስቀባብር፥
የወቅታዊ 'ንጂ የሌለው የዘለቄታ ኅብር፥
ባልና ሚስት የሚያባላ፥ የሚያካክድ ልጅና አባት
የማንም ሚስት የማይሆን፥ ግን የሁሉ እቁባት::
የዋሾነት፥ የሸፍጥ፥ የመሰሪነት መዲና፥
ለጨካኞች ፈውሰ-ንፋስ፥ ለሩህሩሃን ዷና፥
ጊዝያዊ ሽርክና 'ንጂ ቋሚ ዝምድና የሌለው፥
ሽምጣኝነት የበከለው፥ ይሉኝታ የጎደለው፥

አወይ ገልበጥባጣው እስስት፥ ዋ! ፖለቲካ!
ሃቀኛን የሚያረግ የተረሳ ላንቲካ፥
ቅኑን፥ ታኝኮ የተተፋ ማስቲካ::

የዲያብሎስ ውዳሴ ዘያሪ፥
በየካልኢቱ እንደጥላ ተቀያያሪ፥
ተሽከርካሪ እንደ ሰዓት ቆጣሪ፥
የሸር፥ የደባ፥ የሴራ ፈጣሪ፥
ክብረ-ቢስ አቃጣሪ፥
ያረጀች ሴት-አዳሪ፥
እናት-አይምሬ፥ ያባት ተገዳዳሪ::
ይቅር የማይል ቢሠሩ ስተት፥
የማይተማመኑበት ሙልጭልጭ ክስተት፥
የሚጓዝ ጭኖ የተውሳክ ዝተት፥
ለእንስፍስፎች ሃሞት፥ ላረመኔዎች ጣፋጭ ወተት::

የሚያስፈስስ የግፍ ደም አበላ፥
ልቡን ላደነገየ፥ ጎሊናውን ሽጦ ለበላ፥
ለአፈኛ መልካም ጦማር፥
ለሞላጫ ሽጋ ቁማር፥
ለስልጣን ጥመኛ ወለላ ማር፥

የወንጀለኞች መታጎሪያ÷
የአድርባዮች መናኸሪያ÷
የፈላጭቆራጭ ባሪያ÷
የግፈኞች የበደል መሣሪያ÷
የሚለዝብ ለሚያወድም ያለአግባብ÷
የሚመች ለሚስለከለክ እንደእባብ÷
ለቀጥተኛ ነበልባል÷ ለጠማማ ወቅታዊ ድባብ÷
የሚሰምር ለሚወድ አተካራ÷
ገርገሩን የሚያርድ ካራ።

አወይ የዝንታለም ደዌ÷ ዋ! ፖለቲካ÷
አዝጋሚውን የሚያረግ ላንቲካ÷
ልበ-ንጹሁን የሚያረግ የተተፋ ማስቲክ!

የጥቅም ግንኙነት 'ንጂ የሌለው የወዳጅነት ትስስር÷
ከላይ የተከለ አስመስሎ÷ የሚመነጋግል ከስር÷
“ከራስ በላይ ንፋስ” አሰኝቶ÷ የሚያስፈፅም ክህደት÷
በፍቅሩ ለተነደፈ ጨርቅ የሚያስጥል በእብደት።

ምስኪኑን የሚያረግ ሰለባ÷
ክቡሩን የሚያቀል እንደገለባ÷
ጨዋውን የሚያረግ ውሸታም÷
ጭምቱን የሚያረግ ኩሸታም÷
ለተለማጭ ልዝብ÷ ሸካራ ለግትር÷
ለሚያወላውል የመቅሰፍት በትር÷
ለሚዘገይ የሞት መረቅ÷
ለሚፈጥን ሰይፈ-መብረቅ÷
ኮፍጣና ባለመርሆ የማያጎበድድ÷ የማይሰግድለት÷
ተልካሻ አድርባይ ተንበርክኮ የሚያረግድለት÷
በጎ-አድራጊ የሚያስመስል ገፋፊን÷
አፈኛን የሚያስከብር÷ አዋቂ የሚያስመስል ለፍላፊን÷
ትንሹን ትልቅ አድርጎ÷ የታፈረ የሚያስመስል ቀጣፊን።

አወይ ነገረ-መንግስት÷ አወየው! ወዮው! ፖለቲካ!
አዝጋሚን÷አመንቺን የሚያረግ የተረሳ ላንቲካ÷
የዋሁን ተመጦ የተጣለ ሎሚ÷ ቅኑን ታኝኮ የተተፋ ማስቲካ!

መጨበጫ የሌለው ገልበጥባጣ÷ አፏን አሞጥሙጣ
ባንድ ወንድ የማትፅና÷ ሁሉም የሚሸናባት ሸርሙጣ÷
ዐይነደረቅ ሌባ÷ ያሸቀበውን የሚከሰክስ÷
የረከሰውን የሚቀድስ÷ የተቀደሰውን የሚያረክስ÷
የዛሬ ደካሞችን ነገ የሚያረግ ባለአቅመኞች÷
የዛሬን ባንድ አልጋ ተቆራኞች ነገ የሚያረግ ደመኞች÷
ግብረገብነት የማያውቅ÷ የሌለው ሥነምግባር÷
ባንድ አፍ ሰባት ምላስ÷ ለአምባገነኖች ገባር÷
ሠላም÷ ጸጥታ÷ ሃቅን በሚሻ ከቶም የማይታሰብ÷
የሚያበጣብጥ÷ የሚያተራምስ ዘመድ÷ ቤተሰብ÷
በቃኝ ብሎ የመነነን ኮርኩሮ ከገዳም የሚጠራ÷

**በጠጅሳር ታጥነውት የሚከረፋ፥ በናርዶስ የማይጠራ።**
**አውይ ነገረ-መንግሥት፥ አወየው! ወየው ፖለቲካ፥**
**አዝጋሚን፥ አመንቺን የሚያረግ የተሸቀነጠረ ላንቲካ፥**
**የዋሁን ተመጦ የተጣለ ሎሚ፥ ቅኑን ታኝኮ የተተፋ ማስቲካ!**

**እኤአ ጥቅምት** 22 **ቀን** 2007 **ዓ/ም**
**ቫሌሆ፥ ካሊፎርኒያ**